የTJMS IB የወላጆች ዜና

"ራሳችንን፣ የወደፊት ሕይወታችንን እና ዓለማችንን ለማወቅ እና ለማሻሻል አብሮ መማር።"

TJMS ለአገልግሎት ትምህርት ቁርጠኛ ነው

የአገልግሎት ትምህርት እና ስርዓተ ትምህርቱ

ስርዓተ ትምህርቱ የአገልግሎት ትምህርት አቀራራብን በመጠቀም ሲሰጥ፣ ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚማሩትና በማህበረሰቡ ውስጥ በተጨባጭ በሚያጋጥማቸው መካከል እውነተኛ ትስስሮችን ለመገንባት ይችላሉ፡፡ ተማሪዎች **የአገልግሎት ትምህርት** ሒደትን አምስት ደረጃዎች ማለትም ***ምርመራ፣ ዝግጅት፣ እርምጃ መውሰድ፣ ሃሳብን መግለጽና በተግባር ማሳየት፣*** በሚያልፉበት ወቅት፣ ከት/ቤት ባሻገር ባለው "ተጨባጭ ዓለም" ውስጥ ያሉ ፍላጎቶችን ለመሸፈን የሚያስችሉ ጽንሰ ሃሳቦች፣ ክህሎቶችና ዕውቀትን ይተገብራሉ፡፡ በ TJMS ስርዓተ ትምህርት አማካይነት የሚሰጥ የአገልግሎት ትምህርት ምሳሌ የሚሆነው የቤተሰብ እና የሸማቾች ሳይንስ ከስፌትና የሕጻናት ዕድገት ክፍል ጋር በማጣመር ነው፡፡ ተማሪዎች በሕጻናት ላይ የሚደርሱ ድሕረ ጉዳት ስቃዮችን ውጤት በማጥናት በአካባቢው ለሚገኝ መጠለያ በስጦታነት የተበረከቱ "Fear Me Not Monster" አሻንጉሊቶችን ሰርተዋል፡፡

I never perfected an invention
that I did not think about
in terms of the service it might give others . . .
I find out what the world needs,
then I proceed to invent.
Thomas A. Edison, inventor

ገጽ 3 ላይ ይቀጥላል፡፡

የተማሪዎች ማህበረሰብ ፕሮጀክት ፖርቶ ሪኮ ውስጥ በሚገኙ ሴቶች የተዘጋጁ ዕቃዎች ብቅ ባይ መደብር ነው፡፡ ከሽያጭ የሚገኘው ገቢ እዛ ላሉ የሃሪኬን ጉዳት ሰለባዎች ይሰጣል፡፡

የማህበረሰብ ፕሮጀክት

የማህረሰብ ፕሮጀክት ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው የሚተገብሩት የአገልግሎት ትምህርት ሞዴል ነው፡፡ የዚህ ዓመት ፕሮጀክቶች የተለያዩ የማህበረሰብ ፍላጎቶችን በሚፈቱ ግለሰቦችና ቡድኖች አማካይነት በመካሄድ ላይ ናቸው፡፡ በፕሮጀክቱ ውስጥ ከተሸፈኑ አርእስት መካከል የፍልሰተኛና ስደተኛ አድቮኬሲ፣ ቤት አልባነትን መዋጋት፣ የታዳጊዎች ማሕበራዊና አእምሯዊ ጤና፣ በተፈጥሮ አደጋዎች የተጎዱ ማህበረሰቦችን መደገፍና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

የTJMS ቤተሰቦች ማርች 2 ቀን በሚካሄዱ ጉባኤዎች ወቅት የማህበረሰብ ፕሮጀክት የገቢ ማሰባሰቢያዎችን የመደገፍ ዕድል ይኖራቸዋል፡፡



የተማሪዎች የማህበረሰብ ፕሮጀክት አንድን ት/ቤት ተጠቃሚ የሚያደርግ የገቢ ማሰባሰቢያ ነው

የማህበረሰብ ፕሮጀክት ዓላማዎች ተማሪዎች የሚከተሉትን እንዲፈጽሙ ለማበረታታትና ለማብቃት ነው፡

- በዓለም አቀፋዊ አውድ ውስጥ ዘላቂና ራስ-መር በሆነ ምርመራ ውስጥ መሳተፍ
- ፈጠራዊ የሆኑ አዳዲስ ግንዛቤዎችን ለማመንጨትና ጥልቀት ባለው ምርመራ አማካይነት ጥልቅ ግንዛቤን ማዳበር
- አንድን ፕሮጀክት በተራዘመ ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ የሚያስፈልጉ ክህሎቶች፣ አመለካከቶችና ዕውቀትን በተግባር ማሳየት
- በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ውጤታማ የሆነ ግንኙነት ማድረግ
- በትምህርት በኩል ወይም አማካይነት ኃላፊነት የተሞላበትን እርምጃ በተግባር ማሳየት
- የመማር ሒደትን ማድነቅና ባከናወኗቸው ስራዎችም መኩራት፡፡

ተማሪዎች በግንባታ ደረጃም በአገልግሎት ውስጥ ይሳተፋሉ፡፡ የስድስተኛና የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በIB ድረ ገጽ ላይ በአገልግሎት የቀን መቁጠሪያችን ላይ በየሩብ ዓመቱ የሚለጠፉ በርካታ ዕድሎችን እንዲመለከቱ ይበረታታሉ፡፡

በዚህ ዓመት ስፖንሰር የተደረጉ አንዳንድ ዝግጅቶች ለሃሪኬን ሐርቬይ ተጎጂዎች የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ለመሰብሰብ የተደረጉ የመኪና ጉዞዎችን ይጨምራሉ፡፡ ቁሳቁሶቹ ወደ Nationals ስታዲዬም የተወሰዱ ሲሆን ከዚያም ወደ ቴክሳስ ለማጓጓዝ ተጎታች ባላቸው የጭነት መኪኖች ላይ ተጭነዋል፡፡ በተጨማሪም *Wheels to Africa* የሚባል የብስክሌት መሰብሰብ ፕሮግራም ነበረን፡፡



የ TJMS 6ኛና 7ኛ ክፍል ተማሪዎች ከ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የማህበረሰብ ፕሮጀክት ጋር በመተባበር ለ *Wheels to Africa* የተዘጋጀ የብስክሌት መሰብሰብ ፕሮግራም አዘጋጅተዋል፡፡ የ8ኛ ክፍል ተማሪው በአርሊንግተን ካውንቲ የቦርድ ስብሰባ ላይ ፕሮጀክቱን አቅርቧል፡፡ ከላይ፣ ተማሪዎች አሰባሰቡን ለማስተዋወቅ ምልክቶችን አዘጋጅተዋል፡፡ ከታች፣ ተማሪዎች እንዴት ለለጋሾች ሰላምታ እንደሚሰጡ፣ ብስክሌቶችን እንዴት እንደሚፈታቱና ለብስክሌት አሰባሰብ የሚሆኑ ሌሎች ተግባራትን እንዴት እንደሚያከናውኑ የ *Wheels to Africa* ተባባሪ መስራች ከሆኑት Dixie Duncan ሥልጠና እየተሰጣቸው ነው፡፡

በዚህ ዓመት **በኦክቶበር ውስጥ ለተከበረው ልዩነት የመፍጠሪያ ቀን** ተማሪዎች እና ቤተሰቦቻቸው በተለያዩ ተግባራት ውስጥ የተሳተፉ ሲሆን እነርሱም ከ $600 በላይ ያሰባሰብንበት አመታዊው የ Arlington Crop Walk እና በ Culpepper Gardens ውስጥ ለአረጋውያን መቆያ ማቅረብ ናቸው፡፡ ለ **MLK Weekend**፣ ተማሪዎችና ወላጆች እርዳታ ለሚፈልጉ የአርሊንግተን ቤተሰቦች የተዘጋጁ ከ 1,000 በላይ የምርት ከረጢቶችን በማሸግ ረገድ እገዛ አድርገዋል፡፡

የአገልግሎት ትምህርት እና ስርዓተ ትምህርት፣ የቀጠለ

የ8ኛ ክፍል የእንግሊዝኛ እና የዓለም ጂኦግራፊ መምህራን የውሃ ፕሮጀክት ተብሎ የሚጠራ አሳታፊና ተገዳዳሪ የሆነ ባለ ብዙ ዘርፍ ክፍል ለማቅረብ በትብብር መስራታቸውን ቀጥለዋል፡፡ በዚህ ዓመት ልዩ አጽንኦት ተሰጥቶ የነበረው ከመኖሪያ ስለመፈናቀል እና ከመኖሪያቸው የተፈናቀሉ ሰዎች ስለሚያጋጥማቸው አስቸጋሪ ሁኔታ ነው፡፡

“በተለይም የአገልግሎት ትምህርት ሒደቱ ግልጽ ሲደረግ (የአገልግሎት ትምህርት) ተሞክሮ መኖሩ ተማሪዎች የአገልግሎት ሃሳብ በመያዝ ይበልጥ ራሱን የቻለ ተነሳሽነት የመውሰጃ መንገድና ዘዴ አድርገው የሚጠቀሙበት አስተማማኝ ሞዴል ይሰጣል፡፡” (ከ MYP: መርሆዎችን መተግበር፣ 2017)

ተጋባዥ ተናጋሪዎች ተጨባጭ ተሞክሮና ሙያዊ ብቃትን እንዲያጋሩ ተጋብዘው መጥተዋል፡፡ በአርሊንግተን ውስጥ የሚገኘው የስደተኞች ድጋፍ ሰጪ ድርጅት ከሆነው የኢትዮጵያ ኮሙኒቲ የልማት ም/ቤት የመጡት Solace Duncan ሰዎች እንደ ስደተኛ ለመቆጠር እና በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የመኖሪያ ፈቃድ ለማግኘት ስለሚያልፉባቸው አስቸጋሪ ሒደቶች ከተማሪዎች ጋር ተወያይተዋል፡፡ እንዲሁም፣ የ 734 Coffee መስራችና ዳይሬክተር የሆኑት Manyang Kher ከተማሪዎች ጋር ተነጋግረዋል፡፡ Mr. Kher በአንድ ወቅት በጋዜጠኞች እንደሚባለው “የጠፉ የሱዳን ልጅ” ነበሩ። Kher ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ከመምጣታቸው በፊት በስደተኞች ካምፕ ውስጥ ለ16 ዓመታት ቆይተዋል፡፡ ቡናቸው የሚበቅለው ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኘው የጋምቤላ ክልል ሲሆን የሚሸጠው ደግሞ ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ነው፡፡ ከሽያጭ ገቢ ውስጥ ሃያ በመቶ (20%) የሚሆነው ለስደተኞች የእርሻ መሬት፣ ውሃ እና የሙያ ሥልጠና በመስጠት “ትርጉም ያለው እና ከእርዳታ ነጻ” ሕይወት እንዲኖራቸው ለማስቻል ይውላል



አዳዲስ ከ TJMS አገልግሎት የሚጠበቁ ሁኔታዎች

6ኛ ክፍል

- 2 የአገልግሎት ፍላጎት መስኮችን መርጠው ከመማሪያ ክፍል ውጭ ለእያንዳንዱ ቢያንስ በአንድ የአገልግሎት ተግባር ውስጥ ይሳተፉ፡፡
- የ IB አገልግሎት ውጤቶችን ለመሸፈን በ2 ተግባራት ላይ ሃሳብዎትን ይግለጹ፡፡ (ውጤቶቹን በስተቀኝ በኩል ይመልከቱ)
- ለአገልግሎት የእርምጃ መከታተያ እና የማረጋገጫ ቅጽን በመጠቀም የተግባሩን ስፖንሰሮች ፊርማ ያስፈርሙ፡፡

7ኛ ክፍል

- 2 የአገልግሎት ፍላጎት መስኮችን መርጠው ለእያንዳንዱ የፍላጎት መስክ ቢያንስ አንድ የአገልግሎት ተግባር ያላቸው ቢያንስ 3 የአገልግሎት ተግባራት ውስጥ ይሳተፉ፡፡
- ሁለቱም የአገልግሎት ተግባራት ከመማሪያ ክፍል ውጭ መከናወን ያለባቸው ሲሆን ቢያንስ አንድ ተግባር ደግሞ ከት/ቤት ውጭ መከናወን አለበት፡፡
- የ IB አገልግሎት ውጤቶችን ለመሸፈን በተግባራት ላይ ሃሳብዎትን ይግለጹ፡፡ (ውጤቶቹን በስተቀኝ በኩል ይመልከቱ)፡፡
- ለአገልግሎት የእርምጃ መከታተያ እና የማረጋገጫ ቅጽን በመጠቀም የተግባሩን ስፖንሰሮች ፊርማ ያስፈርሙ፡፡

8ኛ ክፍል

- ከአገልግሎት የሚጠበቁ ሁኔታዎች የሚሟሉት በማህበረሰብ ፕሮጀክት አማካይነት ነው፡፡

ተማሪዎች የተሞሉ የሃሳብ መግለጫ መዝገቦችን እና ማናቸውንም ፎቶዎች በዲጂታል የ IB ፖርትፎሊዮ ላይ መጫን አለባቸው፡፡

በመላው ዓለም የሚገኙ የዓለም አቀፍ ባካሎሪያት ት/ቤቶች የአገልግሎት ትምህርት ውጤቶች ተማሪዎች፡-

- *ስለራሳቸው ጥንካሬዎችና መሻሻል ስላለባቸው መስኮች የበለጠ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያስችላሉ*
- *ተማሪ ተኮር ተግባራትን ለመወያየት፣ ለመመዘንና ለማቀድ*
- *አዳዲስ ክህሎቶችን የሚያጎለብቱ ተግዳሮቶችን መወጣት*
- *እርምጃን በጽናት መፈጸም*
- *ከሌሎች ጋር በትብብር መስራት*
- *እርምጃዎቻቸው የሚያስከትሏቸውን ስነ-ምግባራዊ አንድምታዎች ታሳቢ ማድረግ*
- *በዓለም ዙሪያ ተሳትፎ፣ በብዙ ቋንቋ ዕውቀት እና በብዙ ባህል ግንዛቤ በኩል ዓለም አቀፋዊ-አስተሳሰብን ማዳበር*

የአገልግሎት ተግባር መጠናቀቅ የሚረጋገጠው በ TA መምህር ነው፡፡ የሃሳብ መግለጫዎች የሚገመገሙት በ MYP አስተባባሪው ነው፡፡

ሌላ ስኬታማ የአገልግሎት ትርዒት

በአገልግሎት ላይ ትኩረት በማድረግ ዓመቱን ለመጀመር፣ ዓመታዊ የአገልግሎት ትርዒታችንን ለተማሪዎችና ለሠራተኞች የምናካሂደው የአካባቢ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን ለማግኘት እንድንችል ነው። የአካባቢ፣ ሃገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ፍላጎቶችን የሚሸፍኑ ከ 15 በላይ ድርጅቶች ተሳትፈዋል። በርካታ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ለማህበረሰብ ፕሮጀክታቸው ከተሳታፊ ድርጅቶች ጋር አጋርነት ለመፍጠር የተነሳሱ ሲሆን ከእነዚህ ፕሮጀክቶች ተጠቃሚ ከሚያደርጓቸው መካከል: *Turning the Page*፣ *Wheels to African*፣ *Walter Reed 55+ Center*፣ *Teens Making a Difference*፣ እና የአካባቢ የእንስሳ መጠለያዎች ጥቂቶቹ ናቸው። ለሁሉም ተማሪዎች የተዘጋጁ በርካታ ት/ቤት አቀፍ አገልግሎቶች ከትርዒቱ ተገኝተዋል።

ከላይ፣ ተማሪዎች በፊትና አሁን ስላሉ የአረጋውያን ማዕከላት ከአገልግሎት ትርዒት ተሳታፊው *Culpepper Gardens* ገለጻ ይደረግላቸዋል። ከታች፣ ታዳጊ ልጆች *Teens Making a Difference* ወይም *TMAD* በተባለው የአርሊንግተን ፕሮግራም አማካይነት ሌሎች ታዳጊ ልጆችን ለመደገፍ ስለሚያስችሉ ዕድሎች ይማራሉ።

የአገልግሎት ትርዒት ተሳታፊ ድርጅት የሆነው Nothing but Nets በውጭ ሃገር ላሉ ማህበረሰቦች የወባ መከላከያ አጎበር ያቀርባል። እዚህጋ፣ የ TJMS ተማሪዎች የወባ መከላከያ አጎበርን ይሞክራሉ።



ቀኑን ይመዝግቡ!

TJMS IB የማሳያ/የማህበረሰብ ፕሮጀክት ኤግዚቢሽን

ኤፕሪል 17፣ 2018

6:00-7:30pm

ትላልቅ ሃሳቦችን ስለሚዳስሱ፣ ጥልቅ ምርመራን ስለሚያበረታቱ፣ ፈጠራዊነትን ስለሚኮተኩቱና ተማሪዎቻችን ሃሳብ ገላጭ፣ ፈጣሪ እና ጥልቅ አሳቢዎች እንዲሆኑ የሚገዳደሩ ምዘናዎችና የትምህርት ተሞክሮዎችን በተመለከተ ተጨማሪ ግንዛቤ ያዳብሩ።

የ8ኛ ክፍል የማህበረሰብ ፕሮጀክቶችም እንዲሁ ትኩረት ይሰጣቸዋል። ተማሪዎቻችን በአካባቢ፣ ሃገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ማህበረሰቦቻችን ውስጥ እንዴት ልዩነት እንደሚፈጥሩ መጥተው ይማሩ።